# በኢትዮጵያ የመሰረተ-ልማት ስርጭት ፍትሃዊነት ሲፈተሽ

ዶ/ር አዳነ ገበያው ካሳ[i]

በዕውነት ወይም በሃቀኛ መረጃ የተደገፈ ውይይት የአገራችንን ችግር ለመፍታት ከሚያስፈልጉ ተቀዳሚ ነገሮች አንዱ ነዉ። በኢትዮጵያ መሰረተ-ልማትን በፍትሃዊነት ማዳረስ ተገቢ ከመሆኑም አልፎ ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ይረዳል። ዜጎችም ስለ መሰረተ-ልማቱ ስርጭት ግልጽ፣ ተዓማኝና ወቅታዊ መረጃ የማግኘት መብት ሊኖራቸው ይገባል።

ከቅርብ ጊዜ ወድህ በአማራዉ ክልል የዳስ ትምህርት ቤቶች መኖራቸው እየተዘገበ ነው። ይህም የአማራ ክልል እንደ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ የጤና አጠባበቅ መስጫ ተቋማት፣ መንገድ እና ንጹህ ዉሃን በተመለከተ ከሌሎች ክልሎች አንጻር ሲታይ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተጠቃሚ ሆኗል ወይ የሚለዉን ጥያቄ እንድናነሳ ያደርጋል? የዚህ ጽሁፍ ዋናዉ አላማ በአሃዛዊ መረጃ ላይ ተመርኩዞ ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ነው።

ኢትዮጵያ ከአለም የመጨረሻወቹ ድሃ አገሮች አንዷ ናት። ህዝቡ ብዙ ያልተሟሉለት መሰረታዊ ነገሮች አሉ። ምንም አንኳ ይህን አብዛኛዉ በችግር ዉስጥ የሚኖር የኢትዮጵያን ህዝብ በቋንቋ በተመሰረተ አስተዳደራዊ ክልል ከፋፍሎ በዚህ መንገድ ማነጻጸር አስደሳች ነገር ባይሆንም፣ በዜጎች መካከል መልካም ግንኙነትን ለማጠናከር አሃዛዊ መረጃውን በግልፅ ለህዝብ ማቅረብና ዕዉነቱን ማሳየት ተገቢ ነው።

ለዚህ ትንተና የዋለው መረጃ ሁሉም የተገኘዉ ከኢትዮጵያ መንግስት ነው። የአገልግሎቶቹን ስርጭት ፍትሃዊነት ለመመዘን እያንዳንዱ ክልል ከኢትዮጵያ ህዝብ ስንት በመቶዉን ይዟል የሚለውን እንደማነጻጸሪያ (benchmark) ተወስዷል። በኢትዮጵያ ፍትሃዊ የአገልግሎትና መሰረተ-ልማት ስርጭት ሊኖር ይገባል። ሆኖም ግን፣ ፍትሃዊነት ማለት እኩልነት ባለመሆኑ፣ መንግስት ከዚህ ተጨማሪ ማነጻጸሪያና አግልግሎቶቹን የማዳረሻ መመዘኛዎች ሊኖሩት እንደሚችልም ይገመታል።

*ሰዕል 1፡ እኩልነት ከፍትሃዊነት ሲነፃፀር*



[ii]

የ2007 (በአዉሮጳዊያን አቆጣጠር) የኢትዮጵያ ህዝብ ቆጠራ (census) አጠራጣሪ ነበር። የህዝብ ቁጥሩ ትክክለኛነቱና ተዓማኝነቱ በኢትዮጵያ ፓርላማ ውስጥ ሳይቀር ጥያቄ ያስነሳ ነበር፣ ነገር ግን ከእሱ የተሻለ አሃዛዊ መረጃ ለጊዜዉ ባለመኖሩ፣ ለዚህ ትንተና ጥቅም ላይ ዉሏል። ምንም እንኳ የህዝብ ቆጠራዉ መረጃ የቆየ በመሆኑና የአሁኑ ህዝብ ቁጥር ቢጨምርም፣ የመቶኛው ስሌቱ ብዙ ለዉጥ አይኖረዉም የሚለዉን ታሳቢ በመድረግ፣ የህዝቡ ብዛት ስርጭት በክልሎች መቶኛዉ ለዚህ ትንታኔ ማነፃፀሪያ ይዉላል።

ለማሳያ ያህል፣ የትምህርት ቤቶች ብዛት፣ የሆስፒታሎች ቁጥር፣ የሆስፒታል አልጋዎች ቁጥር፣ የመንገዶች ርዝመት፣ እና የንጹህ ዉሃ አገልግሎት በየክልሉ ውስጥ ካለው የህዝብ ብዛት በመቶኛ አንፃር እንመልከት።

በ2007 እ.ኤ.አ ህዝብ ቆጠራ መሠረት፣ ከኢትዮጵያ ህዝብ 36.6% የሚሆነው በኦሮሚያ ክልል ሲኖር፣ 23.4% ደግሞ በአማራ ክልል ይኖራል።[iii] የአገልግሎቶቹም ስርጭት በዚሁ አንጻር እንዲሆን ይጠበቃል። ትንተናው በአመዛኙ የአገሪቱን 60% ህዝብ በያዙት በኦሮሚያና በአማራ ክልል ላይ ያተኩራል። ሌሎች ክልሎችም አስፈላጊ በሆነ ቦታ ተጠቅሰዋል።

## ትምህርት ቤቶች፤

በትምህርት ሚኒስተር 2016/17 እ.ኤ.አ አሃዛዊ መረጃ መሰረት፣ በ2009 ዓ.ም 3,393 የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኢትዮጵያ አሉ። በአገሪቱ ከሚገኙት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 1,367 (40.3%) ኦሮሚያ ዉስጥ ይገኛሉ።[iv] ይህ ከማነፃፀሪያው መቶኛ ከ36.6% የበለጠ ነው፡፡ በሌላ በኩል በአማራ ክልል 23.4% የሚሆነው የአገሪቱ ህዝብ የያዘ ቢሆንም፣ በአገሪቱ ካሉት የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 516 (15.2%) ብቻ ነው ያለው። የአማራ ክልል ፍትሃዊ ድርሻዉን ለማግኘት፣ ወይም በአሁኑ ወቅት ሊኖረዉ ወደሚገባዉ 23.4% ለመድረስ ቢያንስ 271 ተጨማሪ አዲስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መገንባት አለበት። በአንጻሩ ግን ኦሮሚያ ካለው ህዝብ ብዛት ሲመዘን ከሚገባው በላይ 125 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉት። ይህ የሚያሳየዉ የአማራዉ ክልል የሚገባዉን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብዛት ያላገኘ መሆኑን ነው።

*ሰንጠረዥ 1፡ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስርጭት በክልሎች*

| Region | Population 2007 Census | | Secondary Schools | | Primary Schools | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | n | % | n | % | n | % |
| **Ethiopia** | **73,750,932** | | **3,393** | | **35,838** | |
| Tigray | 4,316,988 | 5.9% | 215 | 6.3% | 2,156 | 6.0% |
| Afar | 1,390,273 | 1.9% | 34 | 1.0% | 669 | 1.9% |
| Amhara | 17,221,976 | 23.4% | 516 | 15.2% | 8,798 | 24.5% |
| Oromya | 26,993,933 | 36.6% | 1,367 | 40.3% | 14,309 | 39.9% |
| Somali | 4,445,219 | 6.0% | 130 | 3.8% | 1,422 | 4.0% |
| Benishangul Gumuz | 784,345 | 1.1% | 74 | 2.2% | 580 | 1.6% |
| SNNP | 14,929,548 | 20.2% | 751 | 22.1% | 6,651 | 18.6% |
| Gambella | 307,096 | 0.4% | 54 | 1.6% | 289 | 0.8% |
| Harari | 183,415 | 0.2% | 16 | 0.5% | 95 | 0.3% |
| Addis Ababa | 2,739,551 | 3.7% | 214 | 6.3% | 764 | 2.1% |
| Diredewa | 341,834 | 0.5% | 22 | 0.6% | 105 | 0.3% |

በኢትዮጵያ 35,838 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ፣ 14,309 (39.9%) ያሉት በኦሮሚያ ክልል ሲሆን፣ 8,798 (24.5%) ያሉት ደግሞ በአማራ ክልል ዉስጥ ነዉ። ኦሮሚያ 3.3 መቶኛ ነጥብ ከማንጻጸሪያው በላይ ሲኖረው፣ የአማራው ክልል ያለው 1.1 መቶኛ ነጥብ ከማንጻጸሪያው በላይ ነው። በዚህም መመዘኛ የአማራው ክልል የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ድርሻ ከኦሮሚያዉ ያነሰ ነው።

በኢትዮጵያ ዉስጥ ካሉት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ 11,963 ወይንም አንድ ሶስተኛወቹ ኤሌክትሪሲቲ አላቸው። ከነዚህም 30.4% ኤሌክትሪሲቲ ያላቸው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙት በኦሮሚያ ነው። በአማራ ክልል ኤሌክትሪሲቲ ያላቸው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ድርሻ 13.1% ነው። የኦሮሚያ ክልል ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ኤሌክትሪሲቲ አቅርቦት አንጻር ሲታይ ከአማራ ክልል ከፍተኛ ብልጫ አለው። ስለዚህ በትምህርት አገልግሎት አንጻር ሲታይ፣ ከኦሮሚያ ክልል ጋር ሲወዳደር፣ የአማራ ክልል ተገቢውን ድርሻ ካለማግኘቱም አልፎ ተጎጂ ነዉ።

## ሆስፒታሎችና የሆስፒታል አልጋዎች፤

የሆስፒታሎች ቁጥር እና የሆስፒታል አልጋዎች ብዛት ለጤና ተቋማት ዋና አመላካቾች እንደሆኑ በማሰብ ፣ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ በስታቲስቲክስ መስሪያ ቤት ድረገጽ ላይ ያለው መረጃ እንደሚያሳየው፣ የአማራ ክልል በአንፃራዊ ሁኔታ ተጎጂ ነው። ኢትዮጵያ ዉስጥ፣ ከ2003 እስከ 2004 ዓ.ም ባለው ጊዜ፣ 122 በጤና ጥበቃ ስር ያሉ የመንግስት ሆስፒታሎች አሉ። ኦሮሚያ 42 (34.4%) በመንግስት የሚተዳደሩ ሆስፒታሎች ሲኖረዉ፣ የአማራ ክልል ያለው 19(15.6%) ብቻ ነዉ። የኦሮሚያ ክልል፣ የአማራ ክልል ካለው በመቶ እጥፍ በላይ የሆስፒታል ቁጥር አለው። የአገሪቱን ህዝብ 20.2% የየዛዉ የደቡብ ህዝቦች 20 (16.4%)፣ የአገሪቱን ህዝብ 5.9% የየዛዉ የትግራይ ክልል ደግሞ 14 (11.5%) የአገሪቱን ሆስፒታል ቁጥር አላቸው።[v]

*ሰንጠረዥ 2፡ የሆስፒታልና የሆስፒታል አልጋዎች ስርጭት በክልሎች*

| Region | Population 2007 Census | | Hospitals by MOH | | Hospital Beds | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | n | % | n | % | n | % |
| **Ethiopia** | **73,750,932** | | **122** | | **45,034** | |
| Tigray | 4,316,988 | 5.9% | 14 | 11.5% | 3,690 | 8.2% |
| Afar | 1,390,273 | 1.9% | 4 | 3.3% | 385 | 0.9% |
| Amhara | 17,221,976 | 23.4% | 19 | 15.6% | 3,796 | 8.4% |
| Oromya | 26,993,933 | 36.6% | 42 | 34.4% | 9,936 | 22.1% |
| Somali | 4,445,219 | 6.0% | 7 | 5.7% | 168 | 0.4% |
| Benishangul Gumuz | 784,345 | 1.1% | 2 | 1.6% | 196 | 0.4% |
| SNNP | 14,929,548 | 20.2% | 20 | 16.4% | 1,210 | 2.7% |
| Gambella | 307,096 | 0.4% | 1 | 0.8% | 381 | 0.8% |
| Harari | 183,415 | 0.2% | 2 | 1.6% | 453 | 1.0% |
| Addis Ababa | 2,739,551 | 3.7% | 6 | 4.9% | 1,199 | 2.7% |
| Diredewa | 341,834 | 0.5% | 1 | 0.8% | 309 | 0.7% |
| Central (AA) | | | 4 | 3.3% | 23,311 | 51.8% |

በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የሆስፒታል አልጋዎች፣ በኦሮሚያ 22.1% የሚሆኑት የሆስፒታል አልጋዎች ሲኖሩ፣ በአማራ ደግሞ 8.4% ብቻ ይገኛሉ። ምንም እንኳ 52% የኢትዮጵያ የሆስፒታል አልጋወች ያሉት አዲስ አበበ ዉስጥ ቢሆንም፣ የአማራ ክልል ያለው፣ ኦሮሚያ ክልል ካለው አንድ ሶስተኛዉን አካባቢ የአልጋ ብዛት ነው። ይህም የአማራ ክልል በጤናው አገልግሎት ይበለጥ ተጎጂ መሆኑን ያሳያል።

**መንገዶች፤**

እንደ ጤናና ትምህርት አገልግሎት ሁሉ መንገድ ለህዝብ ኑሮ መሻሻል ቁልፍ ነው። መንገድ የሚገነባዉና የሚጠገነው ብዙ በብድርና በእርዳታ የተገኘ የአገር ሃብት ፈሶበት ነው።

*ሰንጠረዥ 3፡ የመንገዶች ስርጭት በክልሎች*

| Region | Population 2007 Census | | Federal Road in KMs | | Asphalt Only in KMs | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | n | % | n | % | n | % |
| **Ethiopia** | **73,750,932** | | **28,032** | | **14,632** | |
| Tigray | 4,316,988 | 5.9% | 2,547 | 9.1% | 2,098 | 14.3% |
| Afar | 1,390,273 | 1.9% | 1,902 | 6.8% | 1,538 | 10.5% |
| Amhara | 17,221,976 | 23.4% | 6,353 | 22.7% | 3,314 | 22.6% |
| Oromya | 26,993,933 | 36.6% | 9,031 | 32.2% | 4,334 | 29.6% |
| Somali | 4,445,219 | 6.0% | 2,552 | 9.1% | 798 | 5.5% |
| Benishangul Gumuz | 784,345 | 1.1% | 707 | 2.5% | 243 | 1.7% |
| SNNP | 14,929,548 | 20.2% | 4,328 | 15.4% | 2,074 | 14.2% |
| Gambella | 307,096 | 0.4% | 521 | 1.9% | 170 | 1.2% |
| Harari | 183,415 | 0.2% | 47 | 0.2% | 37 | 0.3% |
| Addis Ababa | 2,739,551 | 3.7% | | | | |
| Diredewa | 341,834 | 0.5% | | | | |

እንደ ኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መረጃ፣ በ2016 እ.ኤ.አ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በአጠቃላይ 28,032 ኪ.ሜ አስፋልት እና ጠጠር መንገዶች አሉ። ከዚህ ዉስጥ 14,632 ኪ.ሜ አስፋልት ሲሆን 13,400 ደግሞ የጠጠር መንገድ ነዉ።[vi] በአገሪቱ ካለው መንገድ ርዝመት፣ ኦሮሚያ 32.2% ሲይዝ፣ የአማራ ክልል 22.7% ይይዛል። የኦሮሚያ እና የአማራ ክልሎች ከህዝባቸዉ ብዛት አንጻር ሲታይ ያላቸዉ የመንገድ ድርሻ ዝቅተኛ ነው። የትግራግይ ክልል ህዝብ ቁጥር ሲታይ የኢትዮጵያን ህዝብ 5.9% ሲሆን፣ ከአገሪቱ መንገድ ግን 9% ያለው ትግራይ ዉስጥ ነው። አስፋልት መንገድ ተነጥሎ ከታየ፣ 14% የሚሆነው የአገሪቱ አስፋልት እርዝመት ያለዉ ትግራይ ክልል ነው። በዚህም መመዘኛ ቢሆን የአማራ ክልል ያልተገባዉን የመንገድ ድርሻ አላገኘም።

**ንጹህ የመጠጥ ዉሃ፤**

ንጹህ የመጠጥ ዉሃን በተመለከተ፣ በ2007 እ.ኤ.አ ህዝብ ቆጠራው የተሰበሰበዉ መረጃ እናደሚያሳየው፣ የቧንቧ ዉሃ ከሚጠቀመዉ መኖሪያ ቤት ብዛት፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው (2,909,899 ቤቶች) ከግቢው ዉጭ ሄዶ ዉሃ የሚያገኘዉ ነው። ከዚህም 32% ኦሮሚያ ዉስጥ ሲገኝ፣ አማራ ክልል ዉስጥ ያለው 22.6%፣ ትግራይ ክልል 10.8% አላቸዉ። ቀጥሎ ያለው ከፍተኛ ቁጥር (820,504) በግቢ ዉስጥ ያለን

የቧንቧ ዉሃ የሚጋሩት ቤቶች ናቸዉ። ከዚህ ኦሮሚያ 24% ሲኖረው፣ አማራ ክልል 20.5%፣ ትግራይ ክልል 10.1% አላቸው።  በግቢያቸው የግል ቧንቧ ዉሃ ካላቸው 465,298 ቤቶች፣ 25.5% ያሉት ኦሮሚያ ዉስጥ ሲሆን፣ 17.3% አማራ፣ 7.3% ትግራይ ዉስጥ ናቸዉ።[vii]  በዚህም መመዘኛ ቢሆን የአማራ ክልል ከህዝቡ ብዛት አንጻር ሲታይ ከሚገባው በላይ ድርሻ አልያዘም።

*ሰንጠረዥ 4፡ የቧንቧ ዉሃ ስርጭት በክልሎች*

| Region | Population 2007 Census | | All Housing Units | | Tap Inside the House | | Tap in Compound, Private | | Tap in Compound, Shared | | Tap Outside Compound | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | n | % | n | % | n | % | n | % | n | % | n | % |
| **Ethiopia** | **73,750,932** | | **15,103,134** | | **144,040** | | **465,298** | | **820,504** | | **2,909,899** | |
| Tigray | 4,316,988 | 5.9% | 957,684 | 6.3% | 15,783 | 11.0% | 34,046 | 7.3% | 83,201 | 10.1% | 314,349 | 10.8% |
| Afar | 1,390,273 | 1.9% | 235,752 | 1.6% | 3,240 | 2.2% | 7,215 | 1.6% | 10,243 | 1.2% | 34,641 | 1.2% |
| Amhara | 17,221,976 | 23.4% | 3,849,139 | 25.5% | 22,941 | 15.9% | 80,693 | 17.3% | 168,558 | 20.5% | 657,897 | 22.6% |
| Oromya | 26,993,933 | 36.6% | 5,425,093 | 35.9% | 36,527 | 25.4% | 118,454 | 25.5% | 196,987 | 24.0% | 931,761 | 32.0% |
| Somali | 4,445,219 | 6.0% | 648,541 | 4.3% | 7,131 | 5.0% | 4,416 | 0.9% | 10,814 | 1.3% | 55,429 | 1.9% |
| Benishangul Gumuz | 784,345 | 1.1% | 167,750 | 1.1% | 873 | 0.6% | 748 | 0.2% | 2,756 | 0.3% | 26,895 | 0.9% |
| SNNP | 14,929,548 | 20.2% | 2,993,046 | 19.8% | 16,118 | 11.2% | 43,621 | 9.4% | 86,536 | 10.5% | 637,698 | 21.9% |
| Gambella | 307,096 | 0.4% | 63,692 | 0.4% | 912 | 0.6% | 826 | 0.2% | 3,236 | 0.4% | 15,840 | 0.5% |
| Harari | 183,415 | 0.2% | 44,914 | 0.3% | 857 | 0.6% | 4,861 | 1.0% | 9,830 | 1.2% | 11,923 | 0.4% |
| Addis Ababa | 2,739,551 | 3.7% | 628,985 | 4.2% | 36,663 | 25.5% | 162,861 | 35.0% | 236,223 | 28.8% | 178,640 | 6.1% |
| Diredewa | 341,834 | 0.5% | 72,939 | 0.5% | 2,879 | 2.0% | 7,175 | 1.5% | 10,892 | 1.3% | 38,979 | 1.3% |
| ESPECIAL ENUMERATION AREA | | | 15,596 | 0.1% | 114 | 0.1% | 383 | 0.1% | 1,227 | 0.1% | 5,847 | 0.2% |

## ማጠቃለያ፤

ከላይ የተዘረዘረው የኢትዮጵያ መንግስት አሃዛዊ መረጃ እንደሚያሳየው፣ የአማራዉ ክልል ፍትሃዊ ባልሆነ መንገድ ተጠቃሚ አልሆነም። በተቃራኒዉ የአማራዉ ክልል ካለዉ የህዝብ ብዛት አንጻር የሚገባዉን የትምህርትና የጤና አገልግሎት ካላማግኘቱም አልፎ ኢፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተጎጂ ሆኗል።

የኢትዮጵያ ህዝብ እነዚህን እና መሰል እውነቶችን ማወቅ እና ገንቢ ውይይት ማድረግ ይኖርበታል። ተጨባጭ አሃዛዊ መረጃና የሚረጋገጥ የታሪክ ዕዉቀት አገሪቱን በሰላም ለማስቀጠል ይረዳሉ። ከዚያ ዉጭ ግን፣ ሆን ተብሎም ሆነ ባለማወቅ፣ የሚደረግ ክርክርና ንትርክ፣ መሰረተቢስ በመሆኑ ህዝቡን ይከፋፍል እንደሆነ እንጂ ለአገራችን ዘላቂ መፍትሄ አያመጣም።

የህዝብ መገናኛ ብዙሃንም የሚያቀርቡት ዘገባና ዉይይት በተጨባጭ አሃዛዊ መረጃ ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል። ሃላፊነት በጎደለው መንገድ፣ ያለ ተጨባጭ መረጃ ህዝብን በስሜት ማነሳሳትና መቀስቀስ ለግጭት ይዳርጋል አገርንም አደጋ ላይ ይጥላል።

የኢትዮጵያ መንግስት መስሪያ ቤቶችም ተዓማኝ መረጃን፣ ለብዙዉ ህዝብ በሚገባ መንገድ፣ ሊያቀርቡና ተደራሽ ሊያደርጉ ይገባል።  ቁጥሮቹን ብቻ ያለምንም ማነፃፀሪይ ማስቀመጥ በቂ አይደለም። አሃዛዊ መረጃወቹ ከህዝቡ ብዛትና ፍትሃዊነት አንጻር ተመዝነውና ተነፃፅረዉ ሊቀርቡ ይገባል። ህዝቡም በተረጋገጠ መረጃ ላይ ተመርኩዞ በሰላም የመወያየትና የጋራ መፍሄ የመፈለግ ባህሉን ሊያዳብር ይገባል።

[i] Dr. Adane Gebeyaw Kassa, Director of Institutional Research and Planning, Prairie State College, USA
[ii] Adapted from https://smartreading.org/about-smart/equity/
[iii] Central Statistical Agency: http://www.csa.gov.et/census-report/complete-report/census-2007

[iv] Ministry of Education, Education Statistics Annual Abstract, 2009 E.C. (2016/17)
[v] Central Statistical Agency: National-Statistics-Abstract-2012 http://www.csa.gov.et/national-statistics-abstract-2003-15/category/296-national-statistics-abstract-2012
[vi]Ethiopian Roads Authority: Distribution of the Federal Road Network in to Regions and RNMD by 2016.pdf http://www.era.gov.et/web/guest/road-asset/-/document_library_display/9qSu/view/52021/66008?_110_INSTANCE_9qSu_redirect=http%3A%2F%2Fwww.era.gov.et%2Fweb%2Fguest%2Froad-asset%2F-%2Fdocument_library_display%2F9qSu%2Fview%2F52021

[vii] Central Statistical Agency: http://www.csa.gov.et/census-report/complete-report/census-2007